የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA


አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ ህዳር ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No.14
ADDIS ABABA 25th November, 2004


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፱/፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

በአፍሪካ ቀንድ እና በታላላቅ ሐይቆች አካባቢ ሕገ ወጥ፣ ትናንሽና ቀላል የጦር መሣሪያዎች ዝውውርን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የተፈ ረመውን የናይሮቢ ፕሮቶኮል ማጽደቂያ የወጣ አዋጅ... ገጽ. ፪ሺ፱፻፵፯


CONTENTS


Proclamation No. 429/2004

The Sub-regional Nairobi protocol for prevention control and reduction of small arms and light weapons in the great likes region and Horn of Africa Ratification proclamation ..Page 2947


### አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፱/፲፱፻፺፯

**በአፍሪካ ቀንድና በታላላቅ ሃይቆች አካባቢ ህገ ወጥ ትናንሽና ቀላል የጦር መሣሪያዎች ዝውውርን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የተፈረመውን የናይሮቢ ፕሮቶኮል ማጽደቂያ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በአፍሪካ ቀንድ እና የታላላቅ ሐይቆች አካባቢ አገሮች መካከል የሕገ ወጥ፣ ትናንሽና ቀላል የጦር መሣሪያዎችን ዝውውር ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስምምነት ሚያዝያ ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፮ በናይሮቢ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፣

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋይ ሀገሮች ህጐች መሠረት ስምምነቱ በ፪/፫ አገሮች መጽደቁ ከተረጋገጠ በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ በመገለፁ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፪ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### PROCLAMATION NO. 429/2004

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE SUB-REGIONAL NAIROBI PROTOCOL FOR THE PREVENTION CONTROL AND REDUCTION OF SMALL ARMS AND LIGHT WEAPONS IN THE GREAT LIKES REGION AND THE HORN OF AFRICA**

**WHEREAS,** the protocol on the prevention, control and reduction of small arms and light weapons in the Great Likes Region and Horn of Africa is signed among the Governments of the Sub-region in Nairobi 21 April 2004;

**WHEREAS,** it is stipulated in the protocol that it shall enter in to force after the deposit of ratification by two thirds of the member states;

**WHEREAS,** the House of the People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said protocol at its session held on 11th day of November, 2004;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is here by proclaimed as follows;


ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በአፍሪካ ቀንድ እና በታላላቅ ሐይቆች አካባቢ ሕገ ወጥ፣ ትናንሽና ቀላል የጦር መሣሪያዎችዝውውርን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የተፈረመውን የናይሮቢ ፕሮቶኮል ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፱/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ፕሮቶኮሉ ስለመጽደቁ**

በአፍሪካ ቀንድና በታላላቅ ሃይቆች አካባቢ ህገ ወጥ ትናንሽና ቀላል የጦር መሣሪያዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በናይሮቢ ከተማ ሚያዝያ ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም. የተፈረመው የናይሮቢ ፕሮቶኮል ፀድቋል::

**፫. አስፈፃሚ አካል**

የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ፕሮቶኮሉን በበላይነት እንዲያስፈፅም እንዲያስተባብር ሥልጣን ተሰጥቷል::

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከህዳር ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ህዳር ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "The Sub-regional Nairobi protocol for prevention control and reduction of small arms and light weapons in the great likes region and Horn of Africa Ratification proclamation No. 429/2004."

**2. Ratification of the protocol**

The protocol on the prevention, control and reduction of small arms and light weapons in the Great Likes Region and the Horn of Africa signed in Nairobi on 21, April 2004 among Governments of the Sub-region is ratified.

**3. Implementing body**

The Ethiopian Federal Police Commission is here by empowered to coordinate and implement this protocol.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force as of the 25th day of November, 2004.

**Done at Addis Ababa, this 25th day of November, 2004.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**